


# የጠብታ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

**ጎብኚዎች** ከመግባታቸው በፊት ከነርስ ጋር ይገናኙ።

ከጅምሩ ለመከላከል፣ የጤና እንክብካቤ ሠራተኞች/ጎብኚዎች እያሉ እቅርታ ከተደረገላቸው፣ ማስክ እንዲያደርጉ ይጠይቁ።

## ከመግባትዎ በፊት፡



እጅዎን ይታጠቡ ያድርጉ



ጭምብል ያድርጉ



የዓይን መጠበቂያዎን

የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ

## ሌላ መስፈርቶች፡



የግድ ለታካሚ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ። የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።




*የኤሮሶል ማመንጨት ሂደት (AGP)*ን እያከናወናችሁ ከሆነ ከፍ ያለ የመከላከያ ጭንብል ወይም መተንፈሻ መልበስዎን እና በሩን ዝግ መሆነን ልብ ይበሉ። የኤሮሶል ማመንጨት ሂደት ለማከናወን የተቋሙን ፖሊሲ ይከተሉ።



ፈሳሽ ጋር መገናኘት የሚቻል ከሆነ ጋውን እና ጓንቶችን ይልበሱ።

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

Washington State Hospital Association

8/10/2023

Washington State Department of HEALTH

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ታካሚው ከወጣ፣ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱን ያንሱ።**

# የጠብታ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

**መደበኛ ቅድሜ ጥንቃቄ ለሁሉም ታካሚ የሚደረጉ የሁል ጊዜ እንክብካቤ ነው።**

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

***የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ) ማድረግ።***

1. የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ
2. መከላከያ ጋዎን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ
3. መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ።
4. የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ
5. ጓንቶችን ያድርጉ

***የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ***

**የተጠቀማችሁት CAPR/PAPR ከሆነ፣ በትክክል ለማውለቅ የአምራች አጠቃቀም መመሪያዎችን ይከተሉ።**

1. ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።
2. ጋዎን ያውልቁ - ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። በተመሳሳይ ጊዜ ትክሻዎን በመያዝ ከሰውነታችሁ በማራቅ ወደ ታች በመሳብ ያውልቁ።ካወለቃችሁ በኋላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።
3. እንደወጣችሁ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።
4. የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።
5. መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።
6. የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ።

**እንደ የሚከተሉት ሁኔታዎች ለመጠቀም (የተቋሙ ፖሊሲ ይመልከቱ)፦**

- ኢንፍሉዌንዛ
- ማጅራት ገትር
- ትክትክ
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ለሎች የመተንፈሻ ቫይረሶች
- መምፕስ

**የታካሚ ምደባ**

- ታካሚን የግል ክፍል ወስጥ ይመድቡ። የማይገኝ ከሆነ፣ ለጋራ መገልገያ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ምግቦችና ዕቃዎች**

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

**የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ**

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ። ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ክፍልን ማጽዳት**

- ተገቢ ከሆነ የአየር ዝውውር በኋላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት የግል መጋረጃ ቅየራ ጨምሮ መደበኛ የጽዳት ሂደቶች ይካሄዳሉ።

**መሣሪያና አቅርቦቶች**

- ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይቀመጡ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

**ትራንስፖርት**

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። **ታካሚው የቀዶ ጥገና ጭምብል ማድረግ** አለበት።
- አጓጓዥ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ።
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ በመርጨት ያጽዱ።

***በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ቅድሙ ጥንቃቄ ያቋርጡ፡***

***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

**420-588 April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

8/10/2023

Washington State Department of HEALTH